# ከዴንማርክ፣ ኖርዌና ስዊድን ዴሞክራሲ በጎ ነገሮች ምን መማር ይቻላል? ከይድነቅ

በርካታ የፖለቲካ ምርምሮችንና ጥናቶችን ስንቃኝ የ"ዴሞክራሲ" ሃሳብ ትልቁንና ማዕከላዊውን ሥፍራ መያዙን እንገነዘባለን። ዴሞክራሲ – ዴሞክራሲን በሥራ ላይ ማዋል ችግር ነው። በእርግጥ ዴሞክራሲ መፍትሄ ነች። ዴሞክራሲ ተሠርታ ያላላቀች ሂደትም ነች። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን – ዴሞክራሲ - የትምህርት ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ምርምርና ጥናት ከመሆን አልፋ - ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የዋለች ማደናገሪያም ሆናለች። በዚህ ዘመን ብዙዎች ዴሞክራት ለመምሰል ይሞክራሉ። የሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ደግሞ ዴሞክራሲን ሕጋዊ ማድረግ ነው። ይህን ፍላጎትና ፈቃድ በሥራ ላይ የሚያውለው ኃይል፣ በሥርዓት የሚመራው ኃይል የተቀናጀ የሕዝብ መንግሥት ነው።

ስካንዲኔቭያ የምንላቸው ሃገሮች ዴንማርክ፣ ኖርዌና ስዊድን ሲሁኑ ፊንላንድና፣ አይስላንድ፣ የፋሮ ደሴቶች (Faroe Islands)፣ አላንድና ስቫልባርድ ደሴቶች (Aland Islands and Svalbard) እንዲሁም ያን ማዬን (Jan Mayen) ሲጨመሩ ኖርዲክ ሃገሮች (Nordic Countries) ይባላሉ። የስካንዴኒቪያን ሃገሮች ዴሞክራሲ የሰዎችን ቀልብ ከሳበ ቆይቷል። ዴሞክራሲ ፅንሠ-ሃሳብ ነች፣ ባይን አትታይም። ስለማትታየዋ ዲሞክራሲ ማውራት ደግሞ ቀላል ላይሆን ይችላል። ዴሞክራሲ እንዴት ነው የምትተገበረው? እንዴትስ ነው ማህበራዊ ለውጥ ልታመጣ የቻለችው? ዲሞክራሲን አስመልክቶ የተላለፉ ገለጻዎች በርካታ ናቸው። ከነዚሁ ውስጥ አንዳንዶቹ ግልጽ ያልሆኑ ወይም አሻሚዎች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ተለዋዋጭነቷን የሚያስረዱ ናቸው። ሁሉም ግን በጋራ የሚግሩት ነገር አለ። "ዴሞክራሲ መቻቻል ነች" ነች።

የዴሞክራሲን ሥረ-መሠረት ለመረዳት የስካንዴኒቭያን ሀገር ምሁራን የትናንሽ ሃገሮችን የአብሮነት ባህል ሳይቀር ያጠናሉ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ዴሞክራሲን አስመልክቶ ሶስት ትላልቅ መጽሃፍት ለዕትመት በቅተዋል። ሁለቱ በእንግሊዝኛ ነው የተጻፉት (Koch & Ross eds. 1949, Lauwerys ed. 1958)። የስካንዴኒቭያን ዴሞክራሲ አስመልክቶ፣ በተለይም ደግሞ ከፅንሰ-ሃሳብነት ወደ ቁሳካልነት ተለውጣ በርካታ ማህበራዊ ለውጦችን ማምጣት ስለቻለው - ምጣኔ-ኃብታዊው ዴሞክራሲም - በርካታ ጽሁፎች ታትመዋል።

የስካንዴኔቪያውም ሆነ ባጠቃልይ የኖርዲክ ሃገሮች ዴሞክራሲ ከሌሎቹ የምዕራቡ ሀገሮች ዴሞክራሲ የተለየች ባትሆንም ነገር ግን በምጣኔ-ኃብት እድገትና በተመጣጣኝ የሃብት ክፍፍል ዙርያ የጎላ ለውጥ ማምጣቷን ማንም አይክድም። በርግጥ ዴሞክራሲያቸው በሂደት ላይ ስለሆነ ክርክሮችና ሙግቶች አሁንም አሉ። የስካንድኔቭያ ዴሞክራሲ አይነተኛ (model) ነች ሲባል - "ፍፁም ነጥራ የወጣች" - ነች ማለት አይደለም። ይሁንና ግን ከዴንማርክ፣ ኖርዌና ስዊድን ዴሞክራሲ እንደ ምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ በጎ ጎኖች አሉ።

፩. ዴሞክራሲ ምንድን ነች? ዴሞክራሲን ስናስብ ሶስት ነገሮች ከፊታችን ድቅን ይላሉ። እነሱም – ተወካይ (ወኪል) (representative)፣ ህገ-መንግሥታዊ (constitutional)፣ ፖለቲካዊ (political) የሚሉት ናቸው። የመራጩን ፍላጎት ሊያስፈጽም የሚችል ሃቀኛ፣ ትጉህና አደራ ተቀባይ ወኪል ከሌለ ዲሞክራሲን ማሰብ አይቻልም። ህገ-መንግስት ከሌለ ዲሞክራሲም የለም። ልበ ሠፊነት፣ ታጋሽነት፣ የመቻቻልና የመቀባበል ፖለቲካ ሳይሰፍን ዲሞክራሲ እያሉ ማውራት ውሃን ሲወቅጡ መዋል ነው። የሶስቱ አበይት ጉዳዮች ድምር የሆነችው ዴሞክራሲ ዋናው ተግባሯ "ሕዝብን አስማምታ የሁሉም – ለሁሉም - አገልጋይ የሆነ መንግሥት" መመስረት ነው። ሮበርት ዳህል የተባለው የስካንዴኒቭያ ምሁር "ዴሞክራሲ ማለት ድርጅት ለመመስረት አልያም ለመቀላቀል የሚኖረው ነጻነት፣ ሃሳብን የመግለጽ መብት፣ የመምረጥ-መመረጥ መብት፣ ሙያዊ ብቃት ያለው ግለሰብ እመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የማገልገል መብቱ፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ድጋፍና ድምጽ የመሰብሰብ መብት፣ መረጃ የማግኘት መብት፣ ነጻና ሚዛናዊ ምርጫ፣ የመንግሥት ፖሊሲዎች በምርጫውና በሌሎች ጠቃሚ ሃሳቦች ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ማድረግ ናቸው" ይላል።

ዴሞክራሲ ሂደት ነች። "ያለቀች፣ የነጠረች፣ በቂ" - የምትባል ዴሞክራሲ ገና አልመጣችም። አንድ ግለሰብ ተፈጥሮ ካደለችው ሙሉ ነጻነቱ ላይ ቆንጥሮ ለመረጠው የፖለቲካ ተቋም በአደራ ይሰጣል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ማዕከላዊውን የመንግሥት ኃይል ለመቆጣጠር በሃሳብ ይታገላሉ። ኃይላቸው የመረጧቸው ግለሰቦች ናቸው። በብዙሃን ምርጫ ሥልጣኑን የተቆጣጠረው ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች መንግሥት ይመሠርታሉ። የመንግሥት ተቋማት ፖለቲካዊ ውሳኔ ያደርጋሉ። መንግሥት አደራ ተቀባይና አገልጋይ እንጂ በዝባዥና ጉቦኛ አይደለም። በኖርዲክ ሃገሮች ውስጥ አንድ ግለሰብ ከሕጻንነቱ ጀምሮ ግብረገብንና የህግ የበላይነትን በቤቱ፣ በሕጻናት መዋያ፣ በትምህርት ቤት ይማራል። ግለሰቦች የለበሱት ግብረገብነትና ሥነ-ምግባር ሥልጣንን ለግል ፍላጎታቸው ማሚያ እንዳያደርጉ ኅሊናቸውን ይገዛል።

፪. ማህበረሰብ - ምን ያህል ነው ዴሞክራሲያዊ መሆን ያለበት? ማህበረሰቡ ፖለቲካውንና ምጣኔ-ኃብቱን ለማያያዝ ዴሞክራሲን እንደ መርህ ይጠቀማል። "ዴሞክራሲ አትጨበጥም፣ ቢሆንም ግን ልቅ ልትሆን አይገባም" ይላሉ የስካንዴኒቭያን ሃገር ሰዎች። "ዴሞክራሲ በወዥንብርና ሃሰት ታምሳ ድንገት አስመሳይ ሰው እጅ ውስጥ ከገባች ማህበራዊ መብቶች ይደፈጠጣሉ" ብለው ይፈራሉ። ከአስመሳዮች የጠራችው የስካንዴኔቭያን ሃገሮች ዴሞክራሲ ጥንቃቄን አክላ ማህበረሰባዊና ኤኮኖምያዊ ጉዳዮችን እንደ ሰንሠለት አያይዛ የባህል፣ የትምህርትና የህግ ፖሊሲዎችን

መስመር ታሲዛለች። መንግስት የሕዝቦች ነጻነት (liberty) እንዲረጋገጥ የግለሰቦች ነጻነትና መብት ላይ ጥበቃ ይደረጋል። አንድ ግለሰብ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በነጻነት ይሳተፋል። ይህም ማለት በሃገሪቱ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አንድ ግለሰብ ካላንዳች ፍርሃት ችሎታውን ያንጸባርቃል ማለት ነው። ተሳትፎ ካነሰ "ጥቂቶች ደፋር (ተናጋሪ) - ብዙሃን ፈሪ (አዳማጭ)" ይሆኑና ፖለቲካ በማይገባው ሰው እጅ መዳፍ ውስጥ ትወድቃለች። ሰዎች ካላንዳች መሽማቀቅ፣ ይሉኝታና ማስመሰል የሚያደርጉት ንጹህ የፖለቲካ ተሳትፎ በዴሞክራሲ ስም የሚወሰልቱ አስመሳዮችንና ጭብጨባ ወዳድ ፖለቲከኞችን ገለል ያደርጋል።

በኖርዲክና ስካንዴኒቭያን ሃገሮች ውስጥ መንግሥት ማለት ማህበራዊ ጥቅሞችን መልሶ ለመራጮቹ ግልሰቦች እኩል ለማከፋፈል - ንጹህ የፖለቲካ ሥራ የሚከውን አካል ነው። ፖለቲካ በስካንዴኒቭያን ሃገሮች ውስጥ ሥልጣን ላይ መወጣጫ ስውር ገመድ አይደለችም። እርግጥ ገመዷን ካልያዙ የፖለቲካ ሥራን ማካሄድ አይቻልም። ግለሰቦች እኩል ክህሎትና እውቀት ሊኖራቸውም አይችልም። ሰዎች ተመሳሳይ የሆነ ሲቪል፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ኃብታዊና ማህበራዊ ግንዛቤ የላቸውም። ውስጣዊ ባህርይ፣ የግንዛቤ ደረጃና እይታ ከግለሰብ ግለሰብ ያለያያሉ። ፖለቲካ - ችሎታን፣ ብስለትን፣ ትህትናን፣ አርቆ አሳቢነትንና አስተዋይነትን ይጠይቃል። የስካንዴንቪያን ሕዝብ እነዚህ በጎ ምግባሮችggg ከታጠቁ ቆይቷል። የሆነ ሆኖ ግን ይላሉ አንድ ምሁር - "ድምጽ ይቆጠራል ግብዓት ይወስናል" (votes count but resources decide)። ፖለቲካ በመሠሪ ፖለቲከኞች ካልተያዘች ባለሙያ ነች። መሠሪ ፖለቲካ የግል ጥቅምን ማፈሻ አካፋ ነች። የመልካም ፖለቲካ ሚና ችግሮችን ከሥር መሠረቱ ተረድቶ መፍትሄ ማዘጋጀት ነው። ባለሙያ ፖለቲካ እንክርዳዱን እያበጠረች የሚጠቅመውን ባማረ ሳህን ታቀርባለች፣ አቅም ካነሳትም ሕዝቡን ታወያያለች።

፫. በስካንዴኒቭያን ሃገሮች ውስጥ ዴሞክራሲ ምን ይዘት አላት? የፖለቲካ ተሳትፎና የሰዎች እኩልነት (participation and equality) የስካንዴኒቭያው ዴሞክራሲ አንኳር ጉዳዮች ናቸው። ዴሞክራሲ እንዲሁ ተወልዳ እንዲሁ አላደገችም፣ ከፊት ለፊቷ የመጡ በርካታ ጣጣዎችን እየቀረፈች ነው ዘመን የተሻገረችው። የውስጥ መቆራቆሶችና ትርምሶች የደሞክራሲ ቀበኞች ናቸው። የእንግሊዝና የአሜሪካ የፖለቲካ ዴሞክራሲ ውጣ ውረዶች ለስካንዴኒቭያው ሰዎች ተሞክሮ ሆነዋል። ከከበርቴውም ሆነ ከኅብረተሰብዓዊው የምጣኔ ኃብት ሥርዓት ጠቃሚ ጠቃሚውን መርጠው በሥራ ላይ ማዋል መቻላቸው ነው ስካንዴኒቭያኖቹን የእኩልነት ማህበራዊ-ዴሞክራሲ ፍሬ ተመጋቢ ያደረጋቸው። ስካንዴኒቭያኖቹን በማህበራዊ-ዴሞክራሲ (social democracy) የሚታገዘው የምጣኔ ኃብት-ዴሞክራሲ (economic democracy) ወደትረፈረፈ ምርትና ወደተሻለ የኃብት ክፍፍል እያሸጋገራቸው ነው።

፬. የስካንዴኒቭያው ፖለቲካዊ-ዴሞክራሲ (political democracy) ምንድነው? የስካንዴኒቭያው ፖለቲካዊ-ዴሞክራሲ ዋነኛ ዓላማው የፖለቲካ ባህሉን ማሳደግ ነው። ፖለቲካ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ወይንም ፓርላሜንት ውስጥ ህግ ሆኖ ይነደፋል። በመንግሥትነት የተሰየመው ይህን ህግ የሚያስፈጽመው ክንፍ (executive branch) ለፓርላሜንቱ ተጠሪ ነው። ይህ አካል ሥራውን በጥራት ካልሰራ የሕዝብ ተወካዩ ምክር ቤት ሊያስወግደው ይችላል (vote of non-confidence)። የህግ ተርጓሚ ተቋማት (judicial institutions) ለዴሞክራሲው ግንባታ ጉልህ ሚና ባይጫወቱም እንኳን ሲቪል መብቶችን ያስጠብቃሉ። ፖለቲካዊ-ዴሞክራሲ ሕዝቡ የፖለቲካ ተሳታፊ እንዲሆን ታበረታታለች፣ ታነቃቃለች። በምርጫ ጊዜ ብቻ ተሳትፎን ማሳየት በቂ የፖለቲካ ባህልን አይገነባም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ስዊድንና ኖርዌ ውስጥ በአብላጫ ድምጽ ያሸነፉ ነጠላ ፓርቲዎች ወንበሩን የመቆጣጠር ዕድል ተቀናጁ እንጂ በስካንዴኒቭያን ሃገሮች አብዛኛውን ጊዜ ፓርቲዎች በጥምረት ሥልጣን ስለሚይዙ ፉክክሩና ተሳትፎው ከፍ ያለ ነው። ሕዝቡ ማንኛውንም ግልጋሎት ከሙስናና አድሎ ውጭ ከሆኑት ዞኖችና ክፍለ-ሃገሮች ያገኛል። የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ሥልጣኑን ሰብስበው አይዙም፣ በተዋረድ ለተቋቋሙት መስተዳድሮች (local and regional governments) ያከፋፍሉታል። በስካንዴኒቭያን ውስጥ ግብረገብና ፖለቲካ ጎን ለጎን ይሄዳሉ። መንግሥት በየተዋረዱ ያሉ መስተዳድሮችን በታማኝነት በቂ የራስ ገዝ ሥልጣን (autonomy) ያስጨብጣቸዋል። እነዚህ አካላት ሥራቸውን በታማኝነት ይወጣሉ፣ ሕዝቡም ያከብራቸዋል። ይህን የመሰለው ሙሉ የሥልጣን ውክልና (delegation of power) ፌደራላዊ ቅርጽ ከያዙ መንግሥታ ክንውኖች ለየት ይላል።

፭. ማህበራዊ-ዴሞክራሲ እንዴት ይገለጻል? ማህበራዊ-ዴሞክራሲ በቅንነትና በመልካም ስነ-ምግባር በሚከወን ሕዝባዊ ግልጋሎት ይገለጻል። ስነ-ምግባሩ በማህበራዊ ቡድኖችና ግለሰቦች መካከል ያለውን የመደብና አካባቢያዊ ልዩነት (class and regional differences) ያሚሟል። የስካንዴኒቪያው ሰዎች ተመሳሳይ (homogeneity) የመሆናቸው ጸጋ ሰላምን አስገኝቶላቸዋል። ስካንዴኒቭያኖች በቤትም፣ በመሥሪያ ቤትም ሆነ በስብሰባ ቦታ ላይ ባህርያቸው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። መቻቻል የማህበራዊ-ዴሞክራሲው ሁነኛ ነጸብራቆች ናቸው። ማህበራዊ-ዴሞክራሲ ከፖለቲካውና ምጣኔ-ኃብታዊው ዴሞክራሲ በቂ ውጤቶች እንዲፈልቁና መልካም ትስስሮች እንዲያድጉ ትጥራለች። ማህበራዊ-ዴሞክራሲ ባጭሩ መግባባት፣ መተሳሰብና መቻቻል ናቸው። ከጥርጣሬና ከለበጣ ውጭ የሆነው መልካም አንድነታቸው ያገኙትን በሰላም እንዲካፈሉ አድርጓቸዋል። የማህበራዊ-ዴሞክራሲያዊ እሴቶች የሆኑት እኩልነትና ትብብር (equality and solidarity) ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ይልቅ ትልቅ ግምት ይሰጣቸዋል። "የእኩልነት" መርኅ የፖለቲካ ሥራ ብቻ ሆኖ ከተተወ በቶሎ አይተገበርም። "እኩልነት" ማህበራዊ ተግባርም ነው። እኩልነትና አድሎ-የለሽ መልካም ቅርብርቦሽ (equality and equity) የስካንዴኒቭያው ሃገሮች ዓይነተኛ መግለጫ ነው። መልካም ባህርያት ለፖለቲካ

ባህል እድገት አስተዋጾ አላቸው። የነቃ ተሳትፎ ከሌለ ዴሞክራሲ ትቀጭቻለች። ለዚህም ነው ተሳትፎና የሲቪል ሙብቶች መከበር ጎን ለጎን የህገ-መንግስት ጥበቃ የሚደረግላቸው። ዴሞክራሲ አሰስ ገሰሱን አትሰበስብም። ጥሩ ሃሳብ እንዳለ ሁሉ መጥፎ ሃሳብም አለ። ዴሞክራሲ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወረወሩ ሃሳቦችን ታበጥራለች። ዴሞክራሲ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚንጸባረቀውን ማህበራዊ ሕይወት ትመዘናለች። ዴሞክራሲ - ግለሰቡ አንዳንዴ እንደግለሰብነቱ አንዳንዴ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ አባልነቱ እርሷ የሰጠችውን ፍሬ ማጣጣሙንም ትገመግማለች። ከአራቱም አቅጣጫ የሚወረወረው ሃሳብ በጊዜና በሂደት እየተደመረ ለዴሞክራሲ እድገት አስተዋጾ ያደርጋሉ።

ስካንዲኔቭያ ውስጥ ዴሞክራሲ የፖለቲካ መሳርያ (political machine) አይደለችም፣ ይልቁንም ዴሞክራሲ ወደ ማህበራዊ-ዴሞክራሲ (social democracy) የምታሸጋግር ግለሰቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጓዙባት የአብሮነት ድልድይ ነች። የማህበራዊ-ዴሞክራሲ መገለጫዎች፣ እኩልነት (equality)፣ የቦታ፣ የማንነት፣ የሰው ልጅ እኩልነት (equality of status)፣ የመወዳደር፣ የማወቅ፣ የመሳተፍ፣ ወዘተ፣ እኩልነት (equality of opportunity)፣ እንዲሁም እኩሌ እኩሌ ሳይሉ እኩል የማስጀመር (equality of starting) ግቦች ናቸው።

፮. የስካንዴኔቪያ ምጣኔ-ኃብታዊ ዴሞክራሲ ምንድነው? ጂዮቫኒ ሳርቶሪ (Giovanni Sartor) የተባለው ምሁር "ምጣኔ-ኃብታዊ ዴሞክራሲ ማለት ተመጣጣኝ የኃብት ክፍፍልና በምጣኔ ኃብቱ ላይ እኩል የመወሰን ሙብትን (redistribution of welath and equalization of economic opportunities) መቀናጀት ነው" ይላል። ምጣኔ ኃብታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ-ዴሞክራሲው ሌላኛዋ ነጸብራቅ ነች። ፖለቲካ ምጣኔ ኃብቱን ካላሳደገች ቱሪ ናፋ (ባዶ ልፈፋ) ነች። ጫና የማያበዛ መንግሥትና ተሳትፎ የሚያበዙ ትጉህ ግለሰቦች ሲገጣጠሙ ምርት ይትረፈረፋል። ፖለቲካና ምጣኔ-ኃብት በቅንነት ከተያያዙ እድገት ያስገኛሉ። ፖለቲካው በጉቦና ሌብነት ከተመረዘ ምጣኔ-ኃብት ይቀጭጫል ወይንም ይባክናል። መርዘኛ ፖለቲካ አመጽ ትጭራለች።

"ትላልቅ ቤተ ክርስትያኖች - በግርማ ሞገስ ከፍ ብለው፣ ተውበው የሚታዩትን ያህል ዴሞክራሲም እንዲሁ ተደስተው ረክተው በሚታዩ ዜጎች ውስጥ ልትታይ ይገባል" ይላሉ የምዕራቡ ዓለም ሰዎች። ቤተ ክርስትያናት ግብረገብን አስተምረዋል። ዴሞክራሲም የግብረገብ ቅጅ ነች። ዴሞክራሲ የሕዝብ ራዕይ ነች፣ ባለ ራዕዩ ሕዝብም ዴሞክራሲን ይተገብራታል። ስካንዴኒቭያኖች ትልቁ ኃብታቸው የሆኑትን ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ-ኃብታዊና ማህበራዊ-ዴሞክራሲዎቻቸውን በእጅጉ ይንከባከባሉ። ዜጋው አዩኝ አላዩኝ ሳይል በትጋት ይሠራል፣ በትህትና ይነጋገራል። ከላዕላይ መዋቅር እስከ ታኅታይ መዋቅር በተዋረድ የሚያገለግሉት ሁሉ ከሕዝብ በታች መሆናቸውን በአቀራረባቸውና በትህትናቸው ይገልጹታል። በእርግጥ የስካንዴኒቭያው ዴሞክራሲ የተለየ አይደለም፣ እንደማንኛውም ሃገር በሕዝብ ተወካይ በምክር ቤቱ ነው የሚመራው። ስካንዴኒቭያኖቹን ልዩ የሚያደርጋቸው ምናልባት በፍቅር፣ ትብብርና ማህበራዊ ተሳትፎ የዳበረው ፖለቲካዊ ባህላቸው ሊሆን ይችላል። ባለጸጋና በሰው ልጆች ሙብትና እኩልነት የሚያምኑ ዜጎች (affluent and egalitarian) ለመሆን የበቁት ስካንዴኒቪያኖች የስኬታቸው ምስጢር ጽኑ የሆነው መተጋገዛቸውና መቻቻላቸው ነው። ማህበረሰቡ ገንዘቡንና ጉልበቱን እንደችሎታው አፍሶ ተቀራራቢ ጥቅም (benefit) ያገኛል። ዴሞክራሲያቸው እንደ ንጹህ ውሃ ከላይ ከመንግሥቱ መዋቅር እየፈሰሰች እታች ያሉትን ማህበራዊና ምጣኔ ኃብታዊ ጉዳዮችን ታረሰርሳለች። ቅንነት፣ ደግነት፣ መቀባበል፣ መከባበር፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉት የመልካም ባህርያት መገለጫዎች ስካንዲኔቭያ ውስጥ ፍትህ (justice) ከፍ እንድትል ምክንያት ሆነዋል።

ደስታን (happiness) ከፍ ለማድረግና ሙስናን (corruption) ለመቀነስ ብሎም አድሎ የለሽ ማህበራዊ ሕይወትን ማበልጸግ በስካንዴኒቭያ ሃገሮች ውስጥ በሂደት ያሉ ያልተገባደዱ የዴሞክራሲ ሥራዎች ናቸው። ደስታ ማህበራዊ ነች። የተራቡ፣ የታረዙ፣ መጠለያ የሌላቸው ሰዎች አጠገብ የሚኖሩ ባለጠጎች ተፈጥሯዊ ደስታ አይኖራቸውም። የጎረቤታቸው ቤት በላዩ ላይ እየፈረሰበት የሚያዩ ሠፈረተኞች ደስተኞች አይደሉም። ዘርፎ ባለገንዘብ የሆነ ሰው ፍርሃት እንጂ ደስታ በውስጡ የለም። ስካንዴኒቭያ ውስጥ አንዱ እየበላ አንዱ ጦሙን አያድርም። መንግሥት ለተቸገረ ግለሰብ ቤት፣ ልብስ መጠለያ ያቀርባል። ሥራ አጥ ድጎማ ያገኛል፣ ትምህርት፣ ሕክምና፣ የሕጻናት መዋያ፣ የአረጋውያን መኖርያ ነጻ ናቸው። መንግሥት ሁሉም የመኖርያ ቤት ባለቤት እንዲሆን ሥርዓት ዘርግቷል። እነዚህ ሁሉ የሕዝቡ አንድነትና ትብብር የወለዳቸው እሴቶች እንጂ ፖለቲካው ብቻውን የፈጠራቸው አይደሉም። መንግሥትም፣ የፖለቲካ ፓርቲም ይሁን የሠራተኞች ማህበራት አሁን የደረሱበት ማህበራዊ ደስታ ምንጩ ሃይማኖቱ ያዳበረው ትብብርና አንድነት ነው።

በዛም አነሰም ስካንዴኒቭያኖች መሠረታዊ ችግሮችን ቀርፈው ማህበራዊ ደስታ ለብሰዋል። ኖርዲኮች በዓለም የደስታ ሃገሮች (Happiest countries) ሠንጠረዥ ላይ ከአንድ እስከ አስር ባለው ሥፍራ ላይ ይመደባሉ። በ 2019 - Happiest country in 2019 - ፊንላድ አንደኛ ስትሆን ዴንማርክ፣ ኖርዌ፣ አይስላንድ፣ ኔዘርላንድ. ስዊዘርላንድ፣ ስዊድን፣ ኒውዚላንድ፣ ካናዳና አውስትራሊያ በቅደም ተከተል እስከ አስረኛ ያለውን ቦታ ይዘዋል። መቼም ይህ ዓለም አቀፉ የኮቪድ ወረርሽን ደስታቸውን ተፈታተነ እንጂ - Happiest country in 2020 - ሠንጥረዝ ላይ እንደሰፈረው - ፊንላንድ አሁንም አንደኛ ስትሆን ዴንማርክ፣ ስዊዘርላንድ፣ አይስላንድ፣ ኖርዌ፣ ኔዘርላንድ፣ ስዊድን፣ ኒውዚላንድ - በተከታታይ ከሁለት እስከ አስረኛውን ቦታ ይዘዋል። Transparency International በየዓመቱ በሚያወጣው Corruption Perception Index የኖርዲክ አገሮች (Nordic Countries) መቶ በመቶ (100%) ሙስና

አልባ ባይሆኑም ከሞላ ጎደል ሙስና የሌለባቸው (non-corruption) ወይም ፀረ-ሙስና (anti-corruption) ሃገሮች በመባል እስከ አስር ያሉትን ቦታዎች በመያዝ ዓለምን ይመራሉ።

የኖርዲኳ ዴሞክራሲ ለሌሎች ታዳጊ ሃገሮች ተሞክሮ መሆን ትችላለች? ዴሞክራሲያቸው ታጋሽነትን፣ መቀባበልን፣ መቻቻልን፣ መግባባትን በማስተማሩ ረገድ ለአፍሪካ ምሳሌ ልትሆን ትችላለች። የፖለቲካ ተሳትፎን (political participation) ለማሳደግም ከዴሞክራሲያቸው ብዙ መልካም ነገሮችን መቅዳት ይቻላል። የፖለቲካ ተሳትፎ ማለት የሕዝብ ተወካይን መምረጥ (voting representative)፣ በውሳኔ ሕዝብ (referndum) ላይ መስተፍ፣ የፖለቲካ ድርጅትን መፍጠርና በህጋዊው ይሁን ህጋዊ ያልሆነ የተቃውሞ ሰልፍ (legal or illegal protest) ላይ እስከመሳተፍ ያሉትን ሁኔታዎች ያካትታል። ሁልጊዜ የተጠበቀ ውጤት (outcome) ባይመጣም ተሳትፎ ያደረገ ግለሰብ ቢያንስ ቢያንስ መንግሥት ፖሊሲውን እንዲመረምር ማስገደድ በመቻሉ ልቡ ተስፋን (hope) ይሞላል፣ እርካታን (satisfaction) ያዝላል። የፖለቲካ ተሳትፎ መንግስት የተሻለ ፖሊሲ እንዲመርጥና የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ማስገደድ ማለት ነው። የተሻለ ውጤት ማለት - ደስታና እርካታን (happiness and satisfaction) ማፍለቅ ነው። የፖለቲካ ተሳትፎ ግንዛቤን ከመጨመሩ በላይ ግለሰቡ መብቱንና ግዴታውን (rights and duties) እንዲያውቅ ያደርገዋል።

ኖርዲኮቹን ባጠቃላይ ስካንዴኔቪያኖችን ደግሞ በተናጠል ስናስብ "ዴሞክራሲ" ደስታና እርካታ ነች። አፍሪካን ስናስብ ደግሞ ዴሞክራሲ ገና በውል ያልተያዘች ጽንሥ ሃሳብ ነች። አፍሪካ የራሷ ችግር አለባት። ምግብ፣ የመጠጥ ውሃ፣ ልብስ፣ መጠለያ የሌለውንና በፖለቲካ ትርምሶችና መቆራቆዞች ሳቢያ ተጎጂ፣ ተሰዳጅ፣ ተፈናቃይ የሆነን ሕዝብ የፖለቲካ ተሳታፊ ማድረጉ ቀላል አይደለም። ሕዝቡን ቀና ማድረጉና ፊት ለፊት ከተደነቀሩበት ችግር ማላቀቁ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። ዴሞክራሲ - በስሟ ብዙ ተነግዷል፣ ተምረናል የሚሉ ሰዎች ችግር አብኻዎች እንጂ መፍትሄ አቅራቢዎች አልሆኑም። ጥቂት ያልሆኑ ልሂቃን – መስዋዕት - ከመሆን ይልቅ – ተጠቃሚ - ለመሆን ስለሚንደረደሩ ነባራዊ ሁኔታዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን ማዛመድና ማስተሳሰር ባለማቻላቸው አህጉሪቱን ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ ከተዋል። በአፍሪካ የሚገኙ በርካታ ልሂቃን (elites) ሶስቱን ንጥረ-ፖለቲካዎች ማለትም - ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲን - ማምጣት ያልቻሉ - ሶስት ዓይነት ዲግሪዎችን በከንቱ የተሸከሙ፣ በሕዝብ ገንዘብ የተማሩ የሕዝብ ዕዳ ናቸው። መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መራብ፣ መጠማት፣ መገደል፣ መዘረፍ፣ እስር፣ ግርፊያ፣ በዘር መለያየት - የልህቃኑ የፖለቲካ ተሳትፎ (elites political participation) የወለዳቸው አሳፋሪ ተግዳሮቶች ናቸው።

አፍሪካ ሶስት ዓይነት "ልህቅ" አላት። አንደኛው ዓይነት "ልህቅ" በመንደር፣ በሠፈር፣ በመሸታ ቤቶች እየተዘዋወር የሰውን ስብዕና የሚንድ፣ ሃሚታንና ውሸንብርን የሚያስፋፋ፣ ጓደኛሞችን፣ ጓዶችን፣ ፍቅረኛሞችን፣ ወዘተ፣ ሶስተኛ ሰው ሆኖ የሚያጣላ፣ የሰውን ገመና ለማሽተት የሚራወጥ፣ በየቤቱ የተበላውን፣ የተወራውን ለማወቅ ጥያቄና ስለላ የሚያበዛ "ተራ የመሸታ ቤት ልህቅ" ነው። ሁለተኛው ዓይነት "ልህቅ" ትናንሽ እውቀቶችን ተሸክሞ የሰውን አስተሳሰብ የሚያጣምም፣ ከሃቅ ይልቅ ሸፍጥን የሚወድ፣ አነጋገሩንና አለባበሱን አሳምሮ በተለይ ብርሌ ሲጨብጥ ተንታኝና አዋቂ መስሎ አወዛጋቢ ሃሳቦችን የሚተፋ ለሌሎች የመናገር ዕድል የማይሰጥ "የአስተሳሰብና አስተዋይነት ገዳይ ልህቅ" ነው። ሶስተኛው ዓይነት "ልህቅ" ፖለቲካውን ተሸሽጎ ዝንተ ዓመት የተገነባን አብሮነትን፣ መተጋገዝን፣ መቻቻልን የሚንድ ሰዎች በዘርና በጎሳ በተከፋፈሉለት መጠን አድፍጦ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚቃርም፣ የሌሎችን ሃሳብ የማያዳምጥ፣ ምክንያታዊነትን ንዶ ጽንፈኝነትን የሚገነባ፣ በህዝቦች መሃከል ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ "ክፉ ልህቅ" ነው። ሶስቱም ዓይነት ልህቃን ምክንያታዊነትና አመክንዮ በሕዝቡ መሃል እንዳይሰራጩና የሰዎች የፖለቲካ አስተሳሰብና ባህል እንዳያድጉ ያደርጋሉ። በሃሰትና በክፋት የተለወሱ ትርክቶች ሁሉ ሃቅንና እውነትን አጠውላጊ ክፋቶች ናቸው። የደካማ ልህቃን ውጤቶች የሆኑት ክፋቶች እግር አውጥተው በማህበራዊ መገናኛዎች (face book, youtube, Twitter, etc) ሲረጩ መልካምነትን፣ አስተዋይነትን፣ መቻቻልን፣ መተጋገዝን፣ መግባባትን፣ ወዘተ፣ እንደ አንጨቆረር (black hole) ውጠው ያስቀራሉ።

በአፍሪካ ውስጥ ከላይ ከተመለከትናቸው ዓይነት ልህቃን (elite) ይልቅ ተቻችሎ አብሮ የሚኖረው ሕዝብ ብርቱና ዘመን ተሻጋሪ ነው። እንደ ተኩላ የሚያቅበዘብዘው የፖለቲካ ስግብግብነት (political greediness) ከድንፋታ (anger) ጋር ተዛምዶ የገዛ ወገኑ ላይ ክፉና አስፈሪ አውሬ (evil dragon) ሆኗል። ስግብግብነት ድንቁርናን ያብሳሉ፣ በባዶ ትርክት ያንደፋድፋሉ፣ ግጭት ይፈጥራሉ። ልህቃን ስግብግብ፣ ቁጠኛ፣ ተኩላ፣ ክፉ አውሬ ሲሆኑ የሚያሸንፋቸው ተፈጥሮ ባደለው የመቻቻል ዴሞክራሲ የሚኖረው አስተዋዩ መልካም ሕዝብ ነው።

አፍሪካውያን ዴሞክራሲያችንን ከማህበራዊው የመቻቻሉና ችግሮችን አሸንፎ ከመውጣት ዴሞክራሲ (Harmony and Resilience Democracy) ልንጀምር ይገባል። መልካም የሆኑ ልህቃን የግብረገብ ፍሬ የሆኑትን መቻቻል፣ መቀባበል፣ መከባበርን ለብሰው ሕዝቡ የተጋረጠበትን ችግር አሸንፎ እንዲወጣ አብሮነት ባህል ላይ ቢሰሩ የፖለቲካ ተሳትፎ ያድጋል። አንድ ግለሰብ የፖለቲካ ፓርቲ ከመመስረቱ በፊት እርሱ ራሱ ልበ ሠፊ፣ ታጋሽ፣ ትሁት፣ አርቆ አሳቢ መሆኑን ሊመረምር ይገባል። አስተዋይነት በሂደት ታድጋለች። ይበልጥ አስተዋይ የፖለቲካ መሪ በእርሱ ምክንያት ሕዝብ እንዳይጎዳ አስቀድሞ ይጠነቀቃል። ሁላችንም ቂም በቀል ቀብረን ወደፊት ልንጓዝ ይገባል።

በሃገራችን ውስጥ በርካታ ቤተ ክርስትያኖች፣ መስጊዶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ይታያሉ። የአማኙና የተማረው ሰው ብዛት ብዙ ነው። የኃይማኖት አስተማሪዎች፣ ቀዳሾች፣ አገልጋዮች፣ ዘማሪዎች ብዙ ናቸው። የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች፣ የዜና ሥርጭቶች እንደ አሸን ፈልተዋል። ይህ ሁሉ እንደመብዛቱ - እነሆ ግብረገብና ሥነ-ምግባር እንደ አክስጂን እስትንፋሶቻችን በሆኑ ነበር። ቤተክርስትያኖች፣ መስጊዶች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት - የመልካም ምሁራን፣ የጀግኖች፣ የበሰሉ ልህቃን፣ የደጋግና የሕዝብ ተቆርቋሪ ሰዎች መፈጠርያ ካልሆኑ ችግር አለ ማለት ነው። በስድሳዎቹና ከዚያ በፊት በነበሩት ዓመታት ጀግንነት፣ ምሁርነትና አዋቂነት መልክ ነበረው። ኋላም ቢሆን በኢሕአፓም፣ በመኢሶንም፣ በሌሎችም ድርጅቶች ሁሉ በፖለቲካ የሚሳተፈው ላመነበት ይሞታል እንጂ ጥቅማ ጥምቅሞችን አያባርርም ነበር። ቀድሞ በኃይማኖተኛው፣ በአስተማሪውና በመንግሥት አገልጋዩ ውስጥ ግብረገብና ሥነ-ሥርዓት ይንጸባረቁ ነበር። ልታይ ልታይ - ማለት ነውር ነበር።

ዲሞክራሲን የሚፈጥሩት ግብረገብና ሥነ-ምግባር ለምን ተናዱ? ችግሩን መርምሮ መፍትሄ ማምጣት የኃይማኖት አስተማሪዎች፣ የምሁራንና የሃቀኛ ልህቃን ኃላፊነት እንጂ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ግዴታ ብቻ አይደለም።

የኦሮሞ ገዳ ባህላዊና ማህበራዊ-ዴሞክራሲ እምቅ ኃብት እንዲሁም ጥንታዊ ሳባዊ እውቀትና ጥበብን ያዘልን - ኢትዮጵያውያን - እንደ አውሮፓው ትላልቅ ካቴድራሎች ከፍ ብሎ የሚታይ ውብ ዴሞክራሲ ለአፍሪካችን ለማበርከት ምን ያንሰናል? ታላላቅ ሃይማኖቶች ክርስትናንና እስልምናን (ሥነ-ምግባርንና ግብረገብን) ቀድመን የተቀበልን ሕዝብ፣ አትንኩኝ ባይ ነጻነቱን አፍቃሪ ሕዝብ፣ እንደምን የአፍሪካ ዴሞክራሲ ምሳሌ መሆን ያቅተዋል?

እግዚአብሄር ሃገራችንን ይጠብቅ፣ አሜን